ታላቁ "የሰላም ሰባኪ"
ፕሮፌሰር መስፍን ሆይ!

እምነትዎ ከጥቁር ድንጋይ የጠነከረ፣ ከሸቦ የከረረ ሁኖ እስካሁን ደርሷል። ዓመታትና ዘመናት እምነትዎን ሊለውጡ ቀርቶ ሊያነቃንቁት አልቻሉም። ምን ጊዜም ቢሆን የማይለወጡ ነዎትና። የእምነትዎ መሠረቶች በታሪካዊ ሐቆችና ማስረጃዎች ቢናዱና ቢሻሩ እንኳን! ምን ጊዜም እምነትዎን አልቀየሩም። እስቲ እምነትዎ ስለሰላምና አመፅ ከሚአስተጋቧቸው ነጥቦች መካከል አንዳንዶቹን ብቻ ልጥቀስ። "አመፅን መሣሪያ አድርጎ ሕዝብን የሚጨቁን ሥርዓትና አስተዳደር በሕዝባዊ አመፅ ተገዶ መደምሰስ የለበትም። ካአመፅም ነፃ በሆነ በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንጂ። ይህ ካልሆነ የአመፅ አዙሪትን ያስከትላል። አመፅ አመፅን ይወልዳልና። አንዱ የአመፅ ሥርዓት በሌላ የአመፅ ሥርዓት እየተተካና እየተፈራረቀ ሳይቋረጥ መቀጠል ይችላልና።"

ክቡር ፕሮፌሰር ሆይ!

አንድ ሕዝብ የሚጨቁነውን ሥርዓት በሰላማዊ መንገድ ለማስወገድ ሲሞክር ሁሌም የሚገጥመው እስራትና ጭፍጨፋ ሆኖ ሲገኝስ!?

ከሰላማዊ ትግል መንደርደሪያዎ ተነስቼ ጥያቄውን ለመመለስ ልሞክር። የአመፅ አዙሪት እንዳይቀጥል ዝም ብሎ መታሰር፣ መደብደብ፣ መገደል ነው? ሕዝብ ያለበት? ጨቋኙ ሥርዓት ማሰርና መጨፍጨፍ ሲሰለቸው በሰላማዊ መንገድ ሥልጣኑን ለሕዝብ ያስረክባል ማለት ነው? ይህ እስኪሆን ድረስ ሕዝብ እየተጨፈጨፈ "በሰላም" መገዛት ግዴታው ይሆናል? ባርነቱን ተቀብሎ መኖር ይጠበቅበታል? መብቱ የተገፈፈና የተረገጠ ሕዝብ በሚጨቁነው ሥርዓት ላይ የሚአነሳው አመፅና ጨቋኙ ሥርዓት በሕዝብ ላይ የሚሰነዝረው አመፅ ልዩነት የላቸውም? ሁለቱም አመፅ ናቸውና። እንደርስዎ የአመፅ ፍልስፍና ከሆነ የጨቋኝ ሥርዓት አመፅና ይሕንኑ የሚቃወምና የሚቋቋም አመፅ በእኩልነት መታየት፣ በአንድ ዓይነት መሥፈርት መመዘን አለባቸው?

"አንተም ተው። አንተም ተው።" ሐቀኛ የአገር ሽማግሌና ገለልተኛ ዳኛ "የማያዳላ ዳኛ" ማለት እርስዎ ነዎት። እርስዎ የሚስገበገቡላት "ኢትዮጵያዊ ጨዋነት" ማለት ይቺ ናት!

የጭቆና ሥርዓት ተገርስሶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና በሕግ የበላይነት መተካት የጀመረው ከአመፅ ነፃ የሆነ ትግል በመካሄዱ ምክንያት ነው? በዛሬ ጊዜ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለሕግ የበላይነት እንደ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚጠቀሱት የሰሜን አሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ጨቋኝ ሥርዓቶችን ለማስወገድ ከፍተኛ ሕዝባዊ አመፅ አካሂደዋል። ለዚህ ሁሉ በፋና ወጊነትና በፈር ቀዳጅነት የሚታወሰው ታሪካዊው የፈረንሳይ ሕዝብ ያካሄደው አመፅ ነው።

ስለዚህ ኋላ ቀር በሆኑ የዓለም ክፍሎች (የሦስተኛው ዓለም አገሮች) የሚከሰቱ ሕዝባዊ አመፆች ጨቋኝ ሥርዓቶችን ደምስሰው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች መተካት ያልቻሉት ለምንድነው?
የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች ጨቋኝ ሥርዓቶችን የሚቀባበሏቸው እንዴትና ለምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነው መመለስ ያለበት። አለበለዚያ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ኋላ ቀር አገሮች የፖለቲካ ችግር የቅዱሳን መፃሕፍትና የሰላም ሰባኪያን እጥረት ነው ወደማለት ያደርሳል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍፁም ሰላማዊ በሆነና ሙሉ ሥነ ሥርዓት በተላበሰ መልክ በዘጠና ሰባት ዓመተ ምሕረት ምርጫ ተሳተፈ። ድምፁ በወያኔ ተሰረቀ። ለምን ብሎ ስለጠየቀ፣ ድምፄ ይከበር ስላለ በአጋዚ ኮማንዶ ጦር ተጨፈጨፈ፣ ታሰረ፣ ተሰቃየ። ይህን ካዩ በኋላ አሁንም በሰላማዊ መንገድ በድጋሚ እንዲጨፈጨፍ ነው የሚመክሩት?

በመጨረሻም እርስዎ እዳሉት ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር። ነገር ግን የጐጠኛው መንግሥት ፍላጐት በለመዳችሁት ቋንቋ አነጋግራችኋለሁ ብሎ ስለመነ መፍትሄው በሚገባው ቋንቋ ማናገር ተገቢ ነው እላለሁ።

ከፍርድ ያውቃል ወጨፎ።
ሐምሌ 27 ቀን 2000 ዓ.ም.
(August 3, 2008)